Co-funded by the European Union

german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

Better Migration Management
Horn of Africa



# በኢትዮጵያ የተሻለ የፍልሰት አመራር መርሃ-ግብር

Better Migration Management
Horn of Africa

## ጠቅላላ ይዘት

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 112 ሚሊን እንደሚሆን ይገ
ታል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 1.2 ሚሊዮን ያህሉ ፍልሰተኞች ፣ ስደ
ተኞች እናጥገኝነት ፈላጊዎች ሲሆኑ እነዚህም ከሶማሊያ፣ ኤርትራ
እና ከደቡብ ሱዳን የመጡ ናቸው(የተባበሩት መንግስታት፣2019)፡
፡ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ከሌላቸው ከእነዚህ ሰዎች መካከል ከ70 ፐር
ሰንት በለይ የሚሆኑት ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች ሲሆኑ ይህም
ኢትዮጵያን በምስራቅ አፍሪካ ብዛት ያላቸው ፍልሰተኞችን በማስ
ተናገድ ሶስተኛዋ ሀገር ያደርጋታል፡፡ ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ የተሻለ
ኑሮን ፍለጋ፣ ከቡድናዊ ፍረጃ ለማምለጥ ወይም ሁለቱንም ተግባ
ራዊ ለማድረግ ወደ ባህረ ሰላጤው አከባቢ ሀገራት፣ ደቡብ አፍሪካ
እና አውሮፓ የሚጓዙ ፍልሰተኞች ዋነኛ መተላለፍያ ማዕከል ናት፡
፡ እንደሚታወቀው ብዙዎቹ ፍልሰተኞች የሚጓዙት መደበኛ ባልሆነ
መንገድ ማለትም ቪዛ ወይም ህጋዊ ሰነዶች ሳይኖራቸው ነው፡፡ ይህ
ተጋላጭነታቸው በቀላሉ ፍልሰተኞችን ለሚበዘብዙ እና መጠቀሚያ
ለሚያደርጓቸው የወንጀለኞች መረብ በተለይም ለህገወጥ የሰዎች
አዘዋዋሪዎች ኢላማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ወንዶች፣ ሴቶች እና
ህፃናት ከኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚዘዋወሩ ሲሆን
እነዚህም ተገቢው ድጋፍና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ከላይ
ከተገለፁት በተጨማሪም ኢትዮጵያዊያን በዝብዘዋቸው ተጠቃሚ
መሆን በሚፈልጉ ህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች እጅ ወድቀው ተጋላጭ
ሊሆኑ ወደሚችሉበት ወደ መካከለኛው ምስራቅ ይፈልሳሉ፡፡ እንደ

| | |
|---|---|
| Project name | Better Migration Management programme |
| Political Partner in Ethiopia | Ethiopian Anti-Trafficking Taskforce |
| Duration | April 2016 to September 2022 |
| Implementing Partners in Ethiopia | CIVIPOL, Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH, International Organization for Migration (IOM), United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC). Expertise France and the Italian Department of Public Security were also implementing partners in phase I. GIZ heads the implementing partnership. |

ኤ.አ. በ2020 በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፍልሰተኞች በኮቪድ-19 ወረር
ሽኝ ምክንያት ከጉዞዋቸው ተስተጓግለዋል ወይም ወደ ሀገር ለመመ
ለስ ተገደዋል፡፡

በ2016 የአውሮፓ ህብረት እና ጀርመን በአፍሪካ ቀንድ ያለውን የፍ

Implemented by

Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

BRITISH COUNCIL

CIVIPOL CONSEIL

IOM UN MIGRATION

UNODC United Nations Office on Drugs and Crime



ልሰት ጉዳይ ለማሻሻል የተሻለ የፍልሰት አመራር መርሃ-ግብር (ቢ.ኤም.ኤም.ፒ) መስርተዋል፡፡ መርሃ-ግብሩ የኢትዮጵያ መን ግስት ብሄራዊ የፍልሰት ፖሊሲዎችንና ማእቀፎችን በማዘጋ ጀት እና በማሻሻል ረገድ እንዲሁም አካባቢያዊ ፍልሰትን ለማስ ተዳደር የሚያደርገውን ጥረት ያግዛል፡፡  መርሃ-ግብሩ ከልማት በይነ-መንግስታት እና ከአፍሪካ ህብረት ጋር በቅርበት ተባብሮ ይሰራል፡፡

እስካሁን ባደረገችው የስራ እንቅስቃሴ  ኢትዮጵያ ከሀገር ውስጥ የሰዎች ዝውውር እና ድንበር-ዘለል ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ከመግታት አንፃር አንዳንድ ውጤታማ ስራዎችን አከናውናለች፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በ2007 የተባበሩት መንግስታት የተደራጁ ድንበር ዘለል ወንጀሎችን የመከላከያ ስምምነትን እና ተያያዥ የሆነውን የሰዎችን ህገ-ወጥ ዝውውር እና ድንበር-ዘለል ህገ-ወጥ የፍ ልሰተኞች ዝውውርን ፕሮቶኮል አፅድቃለች(ተቀብላለች)፡፡ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ

ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሀገሪቱ አዋጅ ቁጥር 909ኝን በ2015 ስራ ላይ ያዋለች ሲሆን ይህንኑ አዋጅ በተጠናከረ መልኩ በማሻሻል በ2020 በአዋጅ ቁጥር 1178 አፅድቃለች እንዲሁም በ2016 ህገ-ወጦችን በአግባቡ በህግ ለመ ቅጣት የሚያግዝ የምስክር ጥበቃ አካል አቋቁማለች፡፡ የኢትዮ ጵያ ፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ-ሃይል ህገ-ወጥ የሰዎችን ዝውውር እና ድንበር-ዘለል የፍልሰተኞችን ዝውውር ለመግታትና ለተጋላጮች ፍላጎቶች የበለጠ ውጤታማ የሆነ ምላሽ ለመስጠት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ዙሪያ ፍልሰት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ያስ ተባብራል፡፡ ለህገ-ወጥ ዝውውር ተጋላጭ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየትና ለመከላከል ከሚደረገው ጥረት አንፃር ትብ ብራቸውን ለማሻሻል በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ ለህገወጥ ዝውውር ተጠቂዎች እና ተጋላጭ ፍልሰተኞችን ወደ ተገቢው መጠለያ ለመምራት እና የተሻሉ የህግ፣ የህክምና እና የስነልቦና የድጋፍ አገልግሎት እንዲ ያገኙ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጉ ዘንድ ለድንበር ቁጥጥር ባለስል ጣናት፣ የፖሊስ መኮንኖች እና  ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለመሳሰሉት ግንባር ቀደም የስራው ተሳታፊዎች አስፈላጊው ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በቀጣናው ከሚገኙ ሌሎች በርካታ ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ኢትዮ ጵያ ህገ-ወጥ ዝውውርን ለመግታት ከሰጠችው ምላሽ አንፃር ያለ ችበት ደረጃ እጅግ የተሻለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሀገሪቱ  አሁንም የበቃ ጥራት ያላቸው  በቂ ፍልሰት-ተኮር ፖሊሲዎችና ህጎች የሏትም፡፡

ከዚህም ሌላ የሀገሪቱ መሰረተ ልማት፣ ክልላዊ እና ድንበር-ዘለል ትብብሮች  እና እንዲሁም የእውቀትና የክህሎት አመራር መሻሻል ያስፈልጋቸዋል፡፡ እናነዚህን የመሳሰሉ ችግሮች ደህንነቱ እና ህጋዊ ነቱ የተጠበቀ ውጤታማ የፍልሰት አመራርን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶችን ያጓትታሉ፡፡

## የተሻለ የፍልሰት አመራር መርሃ-ግብር የአሰራር ስልትና ተግባራት

የመርሃ-ግብሩ አጠቃላይ አላማ በዘርፉ ስልጣን የተሰጣቸው ብሄራዊ አካላት እና ተቋማት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ስርዓትን የተ ከተለ እና መደበኛ ፍልሰትን እንዲያስተባብሩ ለማስቻልና የሰ ብዓዊ መብቶች-ተኮር የሆነ ስልትን በመጠቀም በአፍሪካ ቀንድ ውስጥና ከእዚሁ አካባቢ ተነስተው የሚከናወኑ ህገ-ወጥ የሰዎችን ዝውውርና ድንበር-ዘለል ፍልሰተኝነትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመከላከልና ለመቀነስ ነው፡፡ ተግባራቱም የሚከናወኑት በሶስት አካላት ተከፍለው ሲሆን እነዚህም ፡- የፍልሰት አመራር፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርና የድንበር-ዘለል ዝውውርን ጉዳይ የሚከታተሉ ውጤታማ ተቋማት እና የመከላከል/ጥበቃ ስራዎች ናቸው፡፡ በኢ ትዮጵያ የተሻለ የፍልሰት አመራር መርሃ-ግብር ስራዎቹን የሚያከ ናውነው ከኢትዮጵያ የፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ-ሃይል እና ከኢሚግሬሽን፣ ዜግነት እና የወሳኝ ሁነቶች ኤጀንሲ ጋር በመ ቀናጀት ነው፡፡

በመርሃ-ግብሩ ምዕራፍ 1 ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ ምዕራፍ 2 ላይ የሚያተኩረው አካባቢያዊ የተቀናጀ የፍልሰት አመራር ስልትን በማጠናከር እና ከመርሃ-ግብሩ የስራ ጊዜ በኋላም ቀጣይ ነትና ዘላቂነት ያለው አሰራርን በማረጋገጥ ዙሪያ ነው፡፡ የመርሃ-ግብሩ ሰራተኞች ውጤታማነትን ለማረጋገጥና የስራ ድግግሞሽን ለማስወገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች አለምአቀፍ ድር ጅቶች እና በአውሮፓ ህብረት እና በሌሎች ሊጋሶች ከሚደገፉ ፕሮጀክቶች ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡

## የፍልሰት አመራር

በለተያየ ደረጃ ላይ በሚገኙ በዘርፉ የመንግስት የስራ አካላት እና በተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ዘንድ የፍልሰት አመራር ስራን



ቁጥራቸው እያደገ የመጣው የኢትዮጵያዊያን ፍልሰተኞች እንደሚታወቀዉ የሚፈልሱት መደበኛ ባልሆነው መስመር ነው፡፡ ይህም ተጋላጭና የህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ተጠቂ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ©GIZ/Mulugeta Gebrekidane

ለማቀናጀት የኢትዮጵያ ፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብርሃ-ይል በአዋጅ ቁጥር 1178 በተደነገገው መሰረት ወደ ብሄራዊ የአጋርነት ጥምረት እንዲሸጋገር መርሃ-ግብሩ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብርሃ-ይል አርአያነት ያለውን አሰራር በመከተል ክልልአቀፍ የፍልሰት አመራር ኮሚቴዎች በአማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ እና በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስታት ተቋቁመዋል፡፡ እነዚህ ዘርፋዊ እና ውጤታማ የትብብር ስርዓቶች የፍልሰት ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እና የጋራ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸውን አካላት ያካተቱ ናቸው፡፡ መርሃ-ግብሩ በአዋጅ ቁጥር 1178 የተካተቱ ማሻሻያዎች ላይ እና በምስክር ጥበቃ ደምብ ላይ በመ ምርኮዝ ብሄራዊ የፍልሰት መመሪያ እና የህግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት በሚያደርገው ጥረት ውስጥ የፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብር-ሃይልን ይደግፋል፡፡ የፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ ሃይል ከኬንያ፣ ሱዳን እና ዩጋንዳ አቻ አካላት ልምድ እና ምርጥ ተሞክሮን ለመለዋወጥ በሰራተኞች ፍልሰት ዙሪያ ውይይት ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም መርሃ-ግብሩ በተባበሩት መንግስታት የወንጀል መከላከልና የወንጀል ፍትህ ኮሚሽን መድረክ ላይ የኢትዮጵያን ተወካይ ተሳትፎን ያመቻቻል፡፡

እንዲሁም መርሃ-ግብሩ በውጭ ሀገራት የሰራተኞች ፍልሰት ጉዳይ ላይ የሚያተኩረውን አዋጅ ቁጥር 923ን በማሻሻል ረገድ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሚያከናውነው ስራ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ በዚህ ረገድ የሚረቀቀው ህግ በኢትዮጵያ እና በሱዳን መካከል ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን ገብቶ ለመስራት የሚደረግን ወቅታዊ የሰራተኞች  ፍልሰት በተመለከተ የተዘጋጀውን የመግባቢያ ስምምነትና የመሳሰሉትን የሁለትዮሽ ስምምነቶችን ምስረታ ያካትታል፡፡ ከዚህ አንፃር የሚከናወኑ ስራዎች የተጠነሱት በመርሃ-ግብሩ ምዕራፍ 1 ሲሆን በምዕራፍ 2 ይተገበራሉ፡ ፡ የሚመቻቸው ስርዓት የኢትዮጵያ የቅጥር ደምቦችን፣ መደበኛ የመግቢያ ስነስርዓቶችን፣ የስራ ቅጥር ህግን፣ የጤና መድህንን እና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ያካትታል፡፡ ከሱዳን ጋር በድንበር-ዘለል ጉዳዮች ረገድ የሚደረገው ትብብር ከወላጆቻቸው የተነጠሉ እና ደጋፊ የሌለቸውን ህፃናት እንዲሁም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ለመከላከል እና ወደ ተገቢው የአገልግሎት ስፍራ እስከ መምራት ጭምር የሚደርስ ነው፡፡



ትዮጵያና ሱዳን መካከል ወቅታዊ የውጭ ሀገር ስራዎችን ሕጋዊ ማድረግን በተመለከተ የተደረገውን ስምምነትና የመሳሰሉትን የሁለትዮሽ ስምምነቶች፡፡ ©GIZ/Wasil Engel

አንዳንድ ጊዜ በወላጆቻቸው የሚተዉ/የሚዘነጉ ተሰዳጅ ህፃናት ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ስራ እንዲፈልጉ ይገደዳሉ፤ይህ ተጋላጭነታቸው ለወንጀለኛ መረቦችና ለህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች ቀላል ኢላማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ህፃናት እንዲዘዋወሩ የሚደረጉት ለስራ፣ ለፆታዊ ብዝበዛ፣ ጉዲፈቻ፣ አስገዳጅ ጋብቻ እና ለመሳሰሉት ሌሎች አላማዎች ነው፡፡



በሰዎች ፀረ-ዝውውር እና በመሳሰሉት ርእሶች ዙሪያ የሚደረጉ ቀጠናዊ ጉባኤዎች/ኮንፈረንሶች በተሳታፊ ሀገራት መካከል ትብብርን ያጠናክራሉ፡፡ ©GIZ/Sari Omer

የተሸለ የፍልሰት አመራር ኢትዮጵያ ከኬንያ እና ከጅቡቲ ጋር ያላትን የድምበር አካባቢ ትብብር ያሳድጋል፡፡ በመስከረም እና ጥቅምት 2020 አዳዲስ የመግቢያ ቦታዎች በሀገራቱ ድምበር አከባቢ የተከፈቱ ሲሆን ይህም የድንበር አቋራጭ መሰረተ ልማትን የሚያሻሽል እና ጠንቃቃ ስርዓትን የተከተለ እና መደበኛ የሆነ የፍልሰት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚያግዝ እንዲሁም የፍልሰተኞችን ህገወጥ ዝውውር እና የውጭ ፍልሰት ጉዳይ በአግባቡ ለመምራት የሚረዳ ነው፡፡

## ህገወጥ የሰዎች ዝውውርና ድምበር-ዘለል ዝውውርን ጉዳይ የሚከታተሉ ውጤታማ ተቋማት

የተሸለ የፍልሰት አመራር የተሻሻሉ የፍልሰት ፖሊሲዎችን እና ህጎችን ከመተግበር አንፃር የተቋማትን ውጤታማነት ያሻሽላል፡፡ መርሃ-ግብሩ የድምበር-ዘለል ትብብሮችን ከማሻሻሉም በላይ በሀገራዊ የህግ አስፈፃሚ ተቋማትና በአቃቢያነ-ህግ መካከል በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ድምበር-ዘለል የሰዎች ዝውውር ጉዳዮች ዙሪያ ያለው ተቋማዊ ትብብር እንዲሻሻል የሚያደርግ ሲሆን ይህም ደረጃውን የጠበቀ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና የማስረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የማቅረብ ስራን ይጨምራል፡፡

ከዚህም ሌላ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች የምርመራዎችንና የክስ አፈፃፀም ስራዎችን ጥራት ያሻሽላል፡፡ ይህም ልዩ ስልጠናን የመስጠት ስርዓትን ስራ ላይ የማዋል እና ማኑዋሎችንና ካሪኩለሞችን ለፍትህ እና የህግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲትዩት፣ ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለኮሌጆች እና የስልጠና ማዕከላት የሚያዘጋጅ ሲሆን ይህም ከጠቅላይ አቃቤ ህግ ፅህፈት ቤት፣ የአቃቤ ህግ ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣ የፌድራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማህበር፣ የወንጀል ምርመራ መምሪያ እና የፌዴራል ፖሊስ ጋር በመተባበር የሚዘጋጅ ነው፡፡ መርሃ-ግብሩ በተጨማሪም ከህፃናት ጥበቃ አንፃር በፀረ-ህገወጥ ዝውውር ዙሪያ ልዩ ስልጠናን የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ጠንቃቃ እና ህጋዊ ፍልሰትን ለማመቻቸት ከድምበር አካባቢ ተቋማት እና ከኢሚግሬሽን አገልግሎት ለሚውጣጡ ባለስልጣናት በተቀናጀ የድንበር አመራር ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል፡፡

## ጥበቃ

የተሻለ የፍልሰት አመራር በኢትዮጵያ ለሚገኙ የህገ-ወጥ ዝውውር ተጠቂዎች እና ተጋላጭ ለሆኑ ፍልሰተኞች የሚደረገውን ድጋፍና ጥበቃ ያሻሽላል፡፡ መርሃ-ግብሩ በአማራ ክልላዊ መንግስት የተፈፀመውንና አግባብነት ያላቸውን መንግስታዊና

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸውን የዝውውር ተጠቂዎችን የመለየት ፣ ለተገቢው ድጋፍ የመምራትና ጥበቃ የማድረግ ስራን ለማሻሻል አስፈላጊውን ትብብር እንዲያጠናክሩ ላለመው የመግባቢያ ሥምምነት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በክልል ደረጃ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎችና ለተጋላጭ ፍልሰተኞች የሚደረገውን ጥበቃ የሚያቀናጅ ማስተባበሪያ መድረክ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተዋናዮች የሚመሰረት ሲሆን ይህም በሚያጋጥሙ ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰራና ተወያይቶ የጋራ መፍትሄ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

አግባብነት ባላቸው ሁሉም ተዋናይ አካላት መርሃ-ግብሩ ሥልጠና የሚሰጥ ሲሆን ይህም የተደራጀ እና በአግባቡ የተዋቀረ የድጋፍ እና የአገልግሎት አቀራረብ የሚሰጥበት ውጤታማ ስርአት እንዲዘረጋ በማስቻል ለህገ-ወጥ ዝውውር ተጠቂዎች በተለይም ለሕፃን ፍልሰተኞች ልዩ ትኩረት በመስጠት ፍልሰተኞች የመጠለያ፣ የህግ ድጋፍ፣ የህክምናና የማህበረ-ሥነልቦና ድጋፍና የመሳሰሉትን ድጋፍና አገልግሎቶችን በተሻለ መልኩ እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

አጋር የሌላቸውና ከወላጆቻቸው የተለዩ ሕፃን ፍልሰተኞች በራሳቸው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ልዩ ጥበቃና የድጋፍ አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሲቪል ማህበረ-ሰብ ድርጅቶች የሚሰጧቸው አገልግሎት እንዲሻሻሉ የስልጠናና የመሳሪያ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ እንዲሁም ደህንነቱ የተረጋገጠና ትክክለኛ ፍልሰት እንዲኖር የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በክልል ማህበረሰብ ድርጅቶች መድረክ ላይ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

በምዕራፍ 1 በተሻለ ፍልሰት መርሃ-ግብር አማካኝነት ለህገ-ወጥ ዝውውር ተጠቂዎችና ተጋላጭ ፍልሰተኞች እንዲሰጡ የታቀዱና የተወሰኑ አቅርቦቶችና አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በ140 አገልግሎት ሰጪዎች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል ይህ መረጃ በድጋፍና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱ ውስጥ የሚገኙ ተዋናዮች እና ለአገልግሎት ሰጪዎች ይሰጣል፡፡

ከዚህም በላይ በልዩ መርሃ-ግብሩ የአስቸኳይ ፍልሰተኞች አገልግሎት ምላሽ መስጫ ማዕከል በጅግጅጋ (ሶማሌ ክልል) የመመስረት አላማ ያለው ሲሆን ማዕከሉም በአካባቢው የሚተላለፉ ተጋላጭ ፍልሰተኞችን የመደገፍ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## የቢ.ኤም.ኤም ውጤቶች ( ሚያዚያ 2016 - መስከረም 2020)

5,530 የአገራት የስራ ክፍሎች የፍልሰትን የተቀናጀ አስተዳደር ለማሻሻል እና ብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲዎችን ፣ ህጎችን እና ድንበር ተሻጋሪ ትብብርን ለማጠናከር ድጋፍ አድርገዋል፡፡

በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምርመራ እና ክስ፣ የተቀናጀ የድንበር አስተዳደር እና ስደተኞችን ወደ አገልግሎት በማስተላለፍ መስክ ለ 1,033 የክልል እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተዋንያን 37 የአቅም ግንባታ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና የስደተኞች መብቶች ዙሪያ በሕዝብ ግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎች 39,314 ሚሊዮን ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡

6,579 ተጋላጭ ስደተኞች በመጠለያ ፣ በመሰረታዊ አገልግሎቶች ፣ በሕክምና ድጋፍ ታግዘዋል (ምዕራፍ 1 ብቻ) ፡፡

የተሻለ የፍልሰት አመራር ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በቅንጅት በመስራት በጉዳዩ ዙሪያ ዘላቂ መፍትሄ የማበጀት አላማ አለው፡፡ መርሃ-ግብሩ ለኢትዮጵያዊያን የፍልሰት ተመላሾች እና በኢትዮጵያ የሚገኙ ፍልሰተኞች ሙያዊ ስልጠና በመስጠትና በስራ እድል ዙሪያ አግባብነት ያላቸውን ድርጅቶች፣ የመንግስት አካላት እና የሲቪል ማህበራት የሚሳተፉበትን የበዙ-ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡ በውይይቱ በኢኮኖሚና ልማት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ አካላት እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡ የተሻለ የፍልሰት አመራርን በመጠቀም የኢትዮጵያ የፀረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብር-ሃይል የወጣት የፍልሰት ተመላሾችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ  ቅጥራቸው ከመንግስት የወጣት ቅጥር ስትራቴጂ ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ያስችለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ መርሃ ግብሩ ከ1991 ጀምሮ ራሱን የቻለ የኢትዮጵያ ክልል በሆነው የሶማሌ ክልል ውስጥ በሀገር ውስጥ ፍልሰተኛ የልደት፣ የጋብቻና የመሳሰሉትን ኩነቶች ከማስመዝገብ አንፃር ያለውን ችግር ለመፍታት የመንግስት መስሪያቤቶች ተደራሽ የሚሆኑበትን መፍትሔም ያመቻቻል፡፡


**Published by** Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

**Registered offices** Bonn and Eschborn, Germany

**Project** Better Migration Management Programme
Rue de la Charité 33 / Liefdadigheidsstraat 33
1210 Bruxelles/Brussels
Belgique/België

**Contact** Sabine Wenz, Programme Director
E-mail: Sabine.Wenz@giz.de
Phase II EUTF website
Phase I EUTF website
GIZ website

**Contact** BMM Regional Office Ethiopia / Djibouti
Pierre.Jaubert@giz.de

**Design/Layout** GIZ/Ira Olaleye

**Photo credits** GIZ

The programme is funded by the European Union and the German Federal Ministry for Economic Cooperation and Development (BMZ).

GIZ is responsible for the content of this publication.

**As at** September 2020, Brussels